ያ ትውልድ

ያ ትውልድ ቅጽ 11 ቁጥር 1 ........................................................................................መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም.

# ከታሪክ ማኅደር

በቅድሚያ በትንሹ የ50 ዓመት መከራና ደም ላልተለያት ሀገራችንና ሕዝባችን ከነችግራችን እንኳን ለ2016 ዓ.ም. አዲስ ዓመት አሸጋገራችሁ እንላለን። ረሃብ፣ ስደት፣ እሥር፣ ግድያ፣ ጦርነርት ወዘተ. ያልተቋረጡ መለያችን ቢሆንም የዘመን መለወጥ ዓመት መድረስ አይቀርምና እንደባህላችን እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንለዋወጣለን። ዛሬ ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ ስናይ አዲስ ዓመት የተሸጋገርነው ዶሮ ሳይሆን ደም እየሸተተን ነው ብንል አልተሳሳትንም። እንደ ፖለቲካ ድርጅት ትንታኔ ባንሰጥም ስለ ሰው ልጅ መከራ፤ እልቂት፤ ፍትህ እጦት ድምጻችንን እናሰማለንና በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን አማራ ላይ ያነጣጠረ የዘር ፍጅት ስናየው የዛሬ 40 ዓመት ፍጅት "ቀልድ?" መስሎ ይታየናል። "ዳግም እንዳይደገም በእኛ ይብቃ" ብለን ብንጮህም ፍትህ አምባገነኖች፣ ዘረኞች፣ ፋሽስቶች እጅ ወድቃ ፊቷን አዙራብን እግዚሆ! እያሰኘችን ነው። በትንሹ በዚህ 5 ዓመት በሀገራችን ያለቀው ሕይወት፣ አካለ ስንኩል ሁነው የቀሩት ታዳጊ ሕጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት፣ ቀላል እንዳልሆነ ህሊና ያለው ይገነዘበዋል።

የትላንቱን ግድያ አንድ ትውልድ መመተር ብለን በታሪክነቱ ብንዘክረው የዛሬው ምን ተብሎ ለታሪክ እንደሚቀመጥ ስናስበው ይዘገንናል። ግና አልፎ ሀገራችን ኢትዮጵያ ሁና ሕዝባችን ሰው ሁኖ በታሪክ ማህደር ይቀመጣል። ከጊዜ በኋላ የገዳይና ተገዳይ፣ የአስገዳይና ተገዳይ፣ የጨፍጫፊና ተጨፍጫፊ ታሪክ መቸቱን ተገን አድርጎ ቀጣይ ትውልድ እንደሚመዘግበው አንጠራጠርም።

"ያ ትውልድ ተቋም" የእኛን ትውልድ ታሪክ በመዘገብ ትምህርት ይሆን ዘንድ በ "ያ ትውልድ ልሳን" ማስነበብ ከጀመርን እነሆ 12 ዓመት ሆኖናል። ይህ ጅምር ሥራ ከዚያ ጨለማ ዘመን በቀጣይነት አሁን የደረስንበትን አጠናክሮ ለመዘገብ መነሻና መሠረት ይሆናል የሚል እምነት ስላለን ዛሬ አዲስ ዘገባ ለማቅረብ ሳይሆን የ "ያ ትውልድ ቅጽ 1 ቁጥር 1" እትማችንን በድጋሚ በማቅረብ በወቅቱ የማነስና የመብዛት ሳይሆን ስንት ቤተሰብን የረበሸና ወቅቱ ሀገር ዛሬ ለደረሰችበት አስከፊ ሁኔታ የራሱ አስተዋጽዖ እንዳበረከተ ግንዛቤ ይወሰድ ዘንድ አቅርበንላችኋል።

ደርግ የዛሬ 38 ዓመት በምህረት ፍቺ ስም ለገደላቸው ወደ አርባ የሚጠጉ ወገኖች የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን የ«ያ ትውልድ ተቋም» መጀመሪያ ቅጽ ቁጥር 1 ልሳን በ"ያ ትውልድ" ስም ለንባብ ማብቃታችን የሰማዕታት ወገኖቻችንን ታሪክ ህያውነትን ለመመስከር ብቻ ሳይሆን ታሪካቸው ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በር ከፍተናልና ለያ ትውልድ ወገኖችና ቤተሰብ አባላት ተስፋን፤ ለወደቁት ወገኖች ቤተሰብ ብርታትና ጽናትን ይስጥልን እንላለን።

ያለፈን ታሪክ በአግባቡ መዘገብ ለአሁኑም ሆነ ለቀጣይ ትውልድ ማጣቀሻ፣ ማወያያ፣ መንደርደሪያ ይሆናልና የያ ትውልድ ወገኖች የራሳችንን ድርሻ እየተወጣን እንገኛለን። በስማ በለው የሚያጠቁንን፣ ቆሻሻ ታሪካቸውን ለመሸፋፈን ጥላሸት የሚቀቡንን ሳንመለከት የተደረገውን ማቅረቡ ብቻ ለእኛ የጊዜውን አስከፊነትና የተከናወነውን ድርጊት ታሪክን ከመመራመር አንጻር ለሚጥሩ ይጠቅማልና እስካሁን ያበረከትነው እንደተጠበቀ ጉዟችን ይቀጥላል።

የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!
ያ ትውልድ ተቋም ለመረጃ ምንጭነት!!!
ያ ትውልድ ተቋም

መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም. (September 30, 2023)

Email : yatewlid@gmail.com
Website http://www.http://www.yatewlid.org
Facebook:- Yatewlid

# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 1 ቁጥር 1 መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም.

## ታሪካችሁ ህያው ነው

መስከረም ወር በሀገራችን ኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን መለወጫ፣ በአደይ አበባ ተውባ፣ በመስቀል ወፍ ታጅባ፤ እሰይ መስከረም ጠባ የሚቃኝላት፤ ዘመድ ከዘመዱ፣ ወዳጅ ከወዳጁ "እንኳን ለአዲሱ ዓመት አሸጋገረን" የሚባባሉበት ወር ነው። ሕፃናትና ወጣቶች ክረምቱን አርፈው ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ደብተር ለብደው፣ እርሳስ ቀርጸው የሚዘጋጁበት ወቅት ነው።

### ጌታቸው ኩምሳ



ጌታቸው ኩምሳ በሲዳሞ ከ/ዞ የኢሕአፓ ኢ/ዞ
Getachew Kumsa Sidamo EPRP IZ

እ...ዮ...ሃ. . . አ...በ...ባ...ዬ . . . አ...በ...ባ...ዬ...መ...ስ...ከ...ረ...ም...ጠ...ባ...ዬ. . . ዜማዎች ወሩን የሚያደምቁበት፣ ሕፃናት በልጅ አንደበት በሆያሆዬ ዜማ፣ በአበባየሽወይ...ለ..ም..ለ..ም...እናትና አባት የሚመርቁበት፣ "ከብረው ይቆዩኝ" የሚሉበት የመስከረም ወር ናት። ያገሬ ሰው መስከረም ይዛ የምትመጣውን በመጠራጠሩ ይመስል ዕንቁ ጣጣሽ ይላታል።

አዎ መስከረም ወር ለያ ትውልድ ብዙ ጣጣ፣ ብዙ ትዝታ አላት። በመስከረም ወር ሁሉም እንዳቅሙ በየቤቱ የመስዋዕት ደም ያፈሳል። የዶሮ፣ የበግ ... ደም። በዓሉን በደስታ ለመቀበል። ብሉልኝ! ጠጡልኝ! ለመባባል። የሥጋ ምንቸት ገብቶ የጎመን ምንቸት እንዲወጣ። መስከረም ወር ለያ ትውልድ የልጆቹ ደም፣ የወጣት እምቦቃቅላ ደም የፈሰሰበት ትዝታ አለበት። የወጣት ልጃገረዶች "ባመት ወንድ ልጅ ወልደው..." ምረቃ ደርግ በየቀኑ ጀግና እየበላ ወቅቱን ትርጉም አሳጥቶታል። ደርግ በዶሮ ፈንታ ወጣት ያነቀበት፤ መስከረም ወር ትውስታ።

መስከረም 02 ቀን 1967 ዓ.ም. የዓፄውን ዘውድ አገዛዝ አስወግዶ በጊዜያዊነት ስም ሥልጣኑን ከሕዝብ የቀማው ወታደራዊው አገዛዝ፣ ደርግ ሥልጣኑን በጨበጠ በሁለተኛው ዓመት መስከረም ወር በኢሕአፓ ላይ ጦርነት አወጀ። ለዚህም በከተሞች እስከ ቀበሌ፤ በየገጠሩም እስከ ወረዳ የተዋቀረ የግድያ ዘመቻ መምሪያ "አብዮታዊ ዘመቻና ጥበቃ መምሪያ" በሚል ተቋቋመ። ከዚህ ወቅት ጀምሮ "ነፃ እርምጃ" በሚል በደርግ ታጣቂ ቡድኖች በተለይ በየከተሞች ግድያ የዕለት ተለት ተግባር ሆኖ እስከ 1970 ቀጠለ። የመንገድ ለመንገድ ግድያው የደም ጥማቱን አላረካው ያለው መንግስቱ ኃ/ማርያም ግድያን በአፈሳ ቀጠለበት። በየአካባቢዎች እስር ቤቶች ተከፈቱ። ወጣቶችና ጎልማሶች ቀንና ለሊት እየተለቀሙ በየእስር ቤቶቹ ታጎሩ። በየአካባቢው እየታፈሱ ከታሰሩት እየተዘገኑ በደርግ ጥይት ተደበደቡ። "ቀይ ሽብር ለዘላለም ይኑር!" የፋሽስቶች መፈክር ሆነ። የሕፃናት ደም አስፈነጠዛቸው። የወጣቶች ደም ሱስ ሆነባቸው። የእናቶች ስቃይ እንደ ቲያትር አዝናናቸው። ደርግና ባንዳዎቹ ወደ ሰው አውሬነት ተቀየሩ። ግድያ፣ ዝሙት፣ ዝርፊያ ቀለባቸው ሆነ። ሀገር ጮኸች፣ እናቶች ለልጆቻቸው የራሄልን እንባ ተነፈጉ። የአባቶች ጀግንነት አቀረቀረ። የመንግስቱ ሽብር ብርቅዬ ትውልድ ፈጀ። ሀገር አለኝታዋን ተነጠቀች። ያን ለሀገሩ፣ ለሕዝቡና ለሰንደቅ ዓላማው ፋና ወጊ የነበረ ትውልድ በፋሽስቶች ተቀበረ።

ዛሬ አዲስ ዓመትን ስናስብ መስከረም ወርን ስናስታውስ ደርግ ቀይ ሽብር ብሎ ትውልድ የመተረበትን ከ1970/72 ዓ.ም. ስምንት ዓመት እስር በኋላ መስከረም 24 ቀን 1978 ዓ.ም. በምህረት ፍቺ ስም የገደላቸውን ሰማዕታት በማስታወስና በመዘከር ነው።

መስከረም ወር ለያ ትውልድ ቤተሰቦች የሀዘን ወር፣ ዝክረ ሰማዕታት ወራቸው ነው። በ1978 ዓ.ም. መስከረም 24 ቀን ደርግ በገመድ እያነቀ የገደላቸው ጀግኖች ቤተሰቦች መስከረም ወርን በመሪር ሀዘን ይቀበሉታል። አደይ አበባዎቹን ፋሽስቱ ደርግ ቀጥፎባቸዋልና። የዘርይሁን እህት ላለፉት 38 ዓመታት መስከረም ወርን ሻማ ለኩሳ ዕንባዋን የምታፈስበት ነው። ለሷ መስከረሟ፣ ለሷ አደዬዋ፣ ለሷ አበባዬ ዘርይሁን ነውና። የኢሕአፓ ልጆች፣ የሲዳሞ ጀግኖች፣ ጀግናው ጌታቸው ኩምሳ ድቅን ይልባቸዋል። ቁመናው፣ እርጋታው፣ ስነ ሥርዓቱ፣ አነጋገሩ፣ አመራሩ ድቅን ሲል መስከረም ወርን የጨለማ ድባብ ያጠላባቸዋል። ካዛንችሶች መስከረም ወር ይረብሻቸዋል ዮሐንስ ግርማቸው፣ ተሻለ ወንድሙ፣ ንጉሴ ዕውነቱ፣ ጌታቸው አሰፋ፣ ዘርይሁን ባንቲ የመሳሰሉ ወንድሞቻቸውን ደም መንግሥቱ ኃ/ማርያም በአንድ ቀን የዓመት በዓል ምሱ አድርጓቸዋልና።

ወደ 18 የሚጠጉ የኢሕአፓ አባላት በፋሽስቱ ደርግ እየታነቁ የተገደሉበት መስከረም 24 ቀን 38ኛ ዓመት የሙት ዓመታቸው። በቤተሰቦቻቸው የሚያቃጭለው የሀዘን ደውል ለኛም ይሰማናል። አልረሳናችሁም እንላለን። የትግል ተወርዋሪ ኮከብ ብለናቸዋል። የሀገር ብርቅዬዎች፣ የጀግና ተምሳሌቶች፣ የኢሕአፓ መሠረቶች ብለናቸዋል። አጥንታችሁ ብዕር ደማችሁ ቀለም ሆኖ ታሪካችሁ ይዘገባል። ደማችሁ ደማችን ነው። ትውልድ ከፍ ከፍ ያደርጓችኋል፣ ዝናችሁ ብቅ ብቅ ይላል። ታሪካችሁ ህያው ነው! እንላቸዋለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ለ 2016 ዓ.ም. አደረሳችሁ እያልን በዚህ አዲስ ዓመት ለያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የአዲስ ዓመት አበባችንን ***“ያ ትውልድ” ቅጽ 11 ቁጥር 1*** ዕትም እናበረክትላችኋለን። የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን “ያ ትውልድ” በቀጣይነት የያ ትውልድ ታሪኮችን፣ ትውስታዎችን፣ ዝክረ ሰማዕታትን፣ መታሰቢያ ባህላትን (የካቲት 66፣ ሜይ ዴይ፣ ማርች 8)፣ ታሪካዊ ቀኖችን (ዐድዋ፣ የካቲት 12፣ ማይጨው፣ ወዘተ) እያስመለከተ ማስነበቡን ይቀጥላል።

«ያ ትውልድ ተቋም» በ1969 ዓ.ም. የዓለም ሠራተኞች ቀን ክብረ በዓል በሰላማዊ ሰልፍ ለማክበር በወጡ ወጣቶችና ሕፃናት ላይ በደርግ አገዛዝ የደረሰውን የአንድ ምሽት ፍጅት በማሰብ፤ በሜይ ዴይ ማለትም ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም የተቋሙ ድረ ገጽ www.yatewlid.org or www.yatewlid.com ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ መደረጉ ይታወቃል። “ያ ትውልድ” ድረ ገጽ ለያ ትውልድ ወገኖችና ቤተሰቦች እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በ«ያ ትውልድ ተቋም» ለያ ትውልድ መታሰቢያነት የተበረከተ የመረጃ ድረ ገጽ ከመሆኑም በተጨማሪ በደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰለባ ለሆኑት ሰማዕታት ስምና ምስል በማካተት፤ ተረስተው እንዳይቀሩ ተንቀሳቃሽ ሀውልት ሆኖላቸዋል።

በኢሕአፓ እየታተመ ይወጣ በነበረው “የዜና መጽሔት” ጥቅምት/ህዳር 1985 ዓ.ም. እንደ ለ.ማ. ምስክርነት *“1978 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ወህኒ ቤትና ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ስለ ሞት ሳይሆን ስለ መፈታት ብዙ የሚወራበት ጊዜ ነበር። በተለይ በ1978 ዓ.ም. ሳይፈታ የቀረው የፖለቲካ እስረኛ በርካታው በልቡ እፈታለሁ የሚል እምነት ነበረው። አንዳንዱ ደግሞ የተወሰነ ጊዜ እስር ቤት ሊቆይ እንደሚችል ይገምት ነበር።*

*መስከረም 23 ቀን 1978 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ግን አንድ ነገር ተከሰተ። ወደ 40 እስረኞች ስማቸው ተጠርቶ ቅዳሜ መስከረም 24 ቀን ስለሚፈቱ እቃቸውን እንዲያዘጋጁ ተነገራቸው። ከ40ዎቹ ውስጥ ወደ 24 የሚጠጉ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ በጀሆቫ ሃይማኖት ጉዳይ የታሠሩ ናቸው።*

*ከተጠሩት ውስጥ የኢሕአፓ አባላት ቁጥር ወደ 16 ነበር። በብዙዎቹ እስረኞች ዘንድ የዚያን ቀን ጥሪ ከእስር ለመለቀቅ መሰለ። ይህም ምክንያት ነበረው። በተለይ የተጠሩት የኢሕአፓ አባላት ቢያንስ ከ8 ዓመታት በላይ የታሰሩ ነበሩና ከ8 ዓመታት እሥር በኋላ ማን ሞት ይጠብቃል? ሌላው ደግሞ ከዚያ በፊት ፋሽስቶች ደርጎች የፖለቲካ እሥረኞችን ሲገድሉ “እቃችሁን ያዙ” አይሉም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ለመለቀቅ አለመሆኑን የገመቱ ነበሩ። ይህም ምክንያት ነበረው። በተለይ የተጠሩት የኢሕአፓ አባላት ብዙዎቹ በድርጅቱ የከተማዎች ወታደራዊ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ በመሆናቸውና አንዳንዶች ደግሞ በድርጅቱ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ላይ የነበሩ ስለነበር (ለምሳሌ ጌታቸው ኩምሳ) ጥሪው ግድያውን የሚያመለክት ነው ብለው ስለፈሩ ነበር።*

*ቅዳሜ መስከረም 24 ቀን 1978 ዓ.ም. ዙሪያቸውን የተሸፈኑ ከራሺያ ለፋሽስቱ ደርግ “ሶሻሊዝም ግንባታ” ተብለው የተለገሱ እስረኛ ማጎሪያ መኪናዎች መጡ። የተጠሩት ሁሉም እቃቸውን ይዘው ወደነዚህ መኪናዎች ውስጥ ገቡ። ያን ቀን ከርቸሌ ውስጥ ከወትሮው የተለየ ጥበቃ ይታይ ነበር። ለመፈታት ቢሆን ኖሮ ከዚያ በፊት እንደዚያ ዓይነት ጥበቃ አልነበረም። ለማንኛውም ወንድሞቻችን ከተፈቱ በኋላ ቢቻል የዚያን ቀን ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ካልቻሉ*

*ደግሞ እሁድ እለት ጠዋት መጥተው መፈታታቸውን እንዲያረጋግጡልን ተባብለን ተሳስመን ተለያየን። አዎን የመጨረሻ መሳሳም። በተባሉት ቀናትም ሆነ እስከመጨረሻው ግን ወንድሞቻችን አልመጡም።“*

በ ”የሚያነቡ እግሮች”፣ በግርማይ አብርሃ፣ 2002 ዓ.ም. ኢ.አ. እንደተገለጸው *“ቅዳሜ መስከረም 24 ቀን 1978 ዓ.ም. ከከርቸሌ ወደ ማዕከላዊ ምርመራ ተወሰዱ። ማዕከላዊ እንደደረሱም በቃል እንደሚፈቱ ተነገራቸው ወደ አንድ አዳራሽ ተሰበሰቡ። ከዚያ በኋላ ግን ሁለት ሁለት ሆነው እየተጠሩ በሰለጠኑ ወታደሮች አማካኝነት እየታነቁ ተገደሉ።”* በዚሁ ዕለት ለህልፈት የተዳረጉትም በጠቅላላው ቁጥራቸው 40 የሚደርስ እሥረኞች ሲሆኑ የሚከተሉት የኢሕአፓ አባላት ይገኙበታል።








ከ15ቀ27 ዘሪሁን በንቲ
H15K27 Zerhiun Benti

1. ጌታቸው ኩምሳ (በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩንቨርስቲ 4ኛ ዓመት ተማሪ የነበረ) በሲዳሞ የኢሕአፓ ኢንተር ዞን ከፍተኛ 15 ታሰሮ ወደ ከርቸሌ የተላከ
2. ዮሐንስ ግርማቸው ከፍተኛ 15 ቀበሌ 27
3. ንጉሴ እውነቱ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 27
4. ዘርይሁን ባንቲ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 27
5. ተሻለ ወንድሙ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 27
6. ጌታቸው አሰፋ ከፍተኛ 15 ቀበሌ 28
7. አምሃስላሴ ጌታነህ
8. ከበረ ኃይሌ
9. ቴዎድሮስ
10. ሙህዲ ከማል
11. ሱሌማን መሃመድ
12. ቴዎድሮስ አስፋው
13. ዘውዱ ኃይለሚካኤል
14. አሰፋ ረጋሳ
15. ሰለሞን ግርማ
16. ተስፋዬ ገብረ ማርያም
17. ዓለም ኪዳኔ
18. አስናቀ ጌታቸው፤ የኢሕአፓ አባል የነበረውና በከፍተኛ 15 እስር ቤት ኮማንደር በመባል የሚታወቀው አስናቀ ጌታቸው በ1970 ዓ.ም. በከፍተኛው እንደታሰረ ከመቅጽበት ወደ “አብዮቱ ካምፕ ተቀላቀልኩ” በማለት የሚያውቃቸውን ጨምሮ በርካታ እስረኞችን በማስያዝ፣ በመግረፍ፣ በማሰቃየትና በማስገደል አሳዛኝ ድርጊት በመፈጸም ሕይወቱን ለማትረፍ ለከፍተኛ 15 ገዳዮች ያላደረገው ጥረት አልነበረም። እነሱም የሚፈልጉትን ያህል ተጠቅመውበት ወደ ከርቸሌ ወረወሩት። በሌሎች ደም ሊያድናት የጓጓላትን ሕይወቱን ደርግ ከላይ ከተጠቀሱት ለድርጅታቸውና ለሀገራቸው ፍጹም እምነታቸውን ጠብቀው ከተሰዉት ጋር ደባልቆ ገድሎታል።

የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!

yatewlid@gmail.com